# አካል ጉዳተኝነትና የፍትህ ተደራሽነት በኢትዮጵያ

ማዕረግ ገ/እግዚሰብሄር

1.አሳታፊ የሆኑ የአካል ጉዳተኛ መብት ትምህርቶችን በመጠቀም ዜጎች ስለ አካል ጉዳተኞች ሰብዓዊ መብት ያላቸውን ግንዛቤ ማሳደግ፣

2.ፍትህን በሚመለከት ግንዛቤ ለመፍጠር በሚዲያ የሚዘጋጁ ፕሮግራሞች ውስጥ ለአካል ጉዳተኞች አሳሳቢ የሆኑ ጉዳዮችን ማካተት፣

3.አካል ጉዳተኞች ተደራሽ በሆነ መልኩ በተለይም ደግሞ ከመንግስታዊ ተቋማት መረጃ የማግኘት መብት እንዳላቸው የሚያረጋግጥ ህግ ማውጣት ተገቢ ነው።

4.ህግ ነክ መረጃዎች ተደራሽ በሆነ መልኩ የሚሰራጩበት መንገድ ቢፈጠርና በዚህ ዙሪያ የተጀመሩ ስራዎችም ተጠናክረው እንዲቀጥሉ፣ የህግ ሰነዶች በተለይም ደግሞ ዋና ዋናዎቹ የሰብዓዊ መብት ሰነዶች በተለያየ መንገድ ለምሳሌ በብሬይል እንዲቀርቡና እነዚህም በተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መንገዶች እንዲደገፉ ማድረግ ተገቢ ነው።

5. የፍትህ ሴክተሩ አካል የሆኑ ፋሲሊቲዎች ተደራሽ መሆናቸውን በተለይም እነዚህ ፋሲሊቲዎች እየተገነቡ ወይም እየታደሱ ከሆነ ማረጋገጥ፣

6.ለምስክሮች እና በፍርድ ቤት ወይም በሌሎች የፍትህ ስርዓቱ አካላት ላይ ተከራካሪ ወገኖች ተገቢ የሆነ ማቆያ እንዲኖራቸው ማድረግ

7. የፍትህ አካላቱ ለአካልጉዳተኞቹ ተደራሽ በሆኑ የመግባቢያ መንገዶች ለምሳሌ የምልክት ቋንቋ፣ ብሬይል ወዘተ...መግባባት ይችሉ ዘንድ እነዚህን ስርዓቶች ማጠናከር ተገቢ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘም ሆነ ከላይ ለተጠቀሱት ችግሮች ጊዜያዊ እና በግለሰቦች ወይም በየተቋማቱ የሚገኙ ባለሞያዎች ፍቃድና ተባባሪነት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን ተቋማዊና ዘላቂ መፍትሄ በማፈላለግ ለመፍታት መሞከር የእነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች መብቶች ከማስከበርና ውጤታማ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ከማድረግም አንጻር ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል።

8. በየሚንስቴር መስሪያ ቤቱም ሆነ በተጠሪ መስሪያቤቶች ውስጥ ተጠሪ የሚሆኑ አካል ጉዳተኝነትን በሚመለከት የሚሰሩ የስራ ክፍሎች ማቋቋም በተለያየ ዘርፍ የአካል ጉዳተኝነት ጉዳይ መካተቱን ለማረጋገጥ ከማስቻሉና በኮንቬንሽኑም ትኩረት የተሰጠው ከመሆኑ አንጻር ይህ ተግባራዊ ቢደረግና ይህንንም ውጤታማ በሆነ መልኩ ማከናወን ይቻል ዘንድ የማካተቻ መመሪያ ማዘጋጀት ተገቢ ነው፡፡

9. አካል ጉዳተኝነትን በሚመለከት የተደራጀና የተቀናጀ የመረጃ አያያዝና ስታስቲካዊ ሲስተሞች በየፍትህ ተቋማቱ ዘንድ እንዲዘረጉ እና እንዲጠናከሩ ማድረግ ጉዳዩ ትኩረት እንዲሰጠውና ማሻሻያ ስራዎችም በእቅድ እንዲከናወኑ ለማድረግ ከሚኖረው ከፍተኛ ሚና አንጻር ሌላው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ያደርገዋል፡፡